# <u>የመገናኛ ብዙሃን እና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2002 ዓ.ም.</u>

ቀጣዩን ምርጫ ተቀባይነት ያለው ግልፅ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለማስቻል በምርጫ ወቅት የመገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኞች የሚመሩበት ዝርዝር የሥነ-ምግባር ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመገናኛ ብዙኃን ከምርጫ አስፈጻሚዎች የሚሰጡ ምርጫ ነክ መልዕክቶችን ሕዝቡ እንዲያውቀው በማድረግ ረገድ ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ በመረዳት፤

በምርጫው ሂደት የመገናኛ ብዙሃንን ተግባራት አስመልክቶ ሚዲያዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎችና፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት የሚመሩበት አንድ የጋራ የሥነ-ምግባር ደንብ በማውጣት ሁሉም አካላት በደንቡ መሠረት አንዱ የሌላውን መብትና ነፃነት አክብረው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

የመገናኛ ብዙኃን ሕዝቡ ስለምርጫ ስርአቱ፣ ስለ ዕጩዎች ማንነትና ስላቀረቡዋቸው ፖለቲካዊ ፕሮግራሞች በቂ መረጃና ዕውቀት እንዲይዝ በድምፅ መስጫ ካርዱ አማካይነት የሚሰጠው ውሳኔ መረጃንና ዕውቀትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን በማገዝ የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ በመረዳት፤

መገናኛ ብዙኃን በዴሞክራሲያዊው የምርጫ ሂደት ውስጥ መራጮችን በማበረታታት፣ ለመራጮች ውሣኔ የሚያግዙ የተሟሉ መረጃዎችን ማቅረብ እንዲችሉና፣ ከመንግሥት ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ራሳቸውን ነፃና ገለልተኛ አድርገው በመንቀሳቀስ ፍትሃዊ፣ ሚዛናዊና ትክክለኛ ሪፖርት ዘገባ ማቅረብ እንዲችሉ፣

የመገናኛ ብዙኃን ወይም ጋዜጠኞች የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አካል በሆነው የምርጫ ሂደት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሙያዊ ሥነ-ምግባርን በተከተለ አኳኋን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

ለጋራ መግባባት ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ውይይቶችና ምክክሮች የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰባቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ

ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. አንቀጽ 59(4)፣ 91(4) እና 110 መሠረት ይህንን የስነ ምግባር ደንብ አውጥቷል።

## አንቀፅ 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባር ደንብ ቁጥር 6/2002 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀፅ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **“መገናኛ ብዙሀን”** ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችንና ብሮድካስቶችን /የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያን/ የሚያካትት ሥራ ነው፡፡

2. **“ምርጫ ህግ”** ማለት የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ነው።

3. **“ቦርድ”** ማለት በምርጫ ህጉ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።

4. **“ምርጫ ነክ መልዕክት”** ማለት ለምርጫ የሚወዳደር ፓርቲ ድምፅ ሰጭዎችን ለማግባባት የሚያቀርበው የምረጡኝ መልዕክቶች እና በተወዳዳሪዎች የሚቀርብ ማንኛውም ትችትና አስተያየት ነው።

5. **“የፖለቲካ ማስታወቂያ”** ማለት ለምርጫ ውድድር የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጣ የሚያስነግረው ማስታወቂያ ነው።

6. **“የፖለቲካ ፓርቲ”** ወይም **“የፖለቲካ ድርጅት”** ማለት ከሕብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንፀባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡

7. **“የምርጫ ወቅት”** ማለት ቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻው

የምርጫ ውጤት በይፋ በቦርድ እስከሚገለፅበት ያለው ጊዜ ነው፡፡

8. **“የምርጫ ዜና ወይም የወቅታዊ ጉዳዮች ዘገባ”** ማለት አገራዊ ወይም ዓለምአቀፋዊ ይዘት ያላቸው ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ምርጫ ነክ ሁነቶች ላይ የሚያተኩር ወይም በእነዚህ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ትንታኔዎችን፣ አስተያየቶችን የሚያካትት ነው።

9. **“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሠጠው አካል ነው።

## አንቀጽ 3. ዓላማ

ይህ የስነ ምግባር ደንብ መገናኛ ብዙሃን ከፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፉ ፖለቲካዊ መልእክቶችን እና ከምርጫ አስፈፃሚ አካላት የሚወጡ መልእክቶችን ለህብረተሰቡ የሚያደርሱበትን እንዲሁም የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከቱ ነፃ እና ገለልተኛ ግምገማዎችና አስተያየቶችን ማቅረብ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት አላማ አለው፡፡

## አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የስነ ምግባር ደንብ ሀገሪቱ ምርጫን አስመልክቶ ዜና፣ ዘገባ፣ ሪፖርት ወይም መረጃ በሚያቀርቡ፣ በሚያስተላልፉ ወይም በሚያሰራጩ ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙኃን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 5. ህግን ስለ ማክበር

ማናቸውም የመገናኛ ብዙኃን ወይም ጋዜጠኛ ሕገ-መንግሥቱን እና ሌሎች የሀገሪቱን ሕጎች ማክበር አለበት።

## አንቀጽ 6. የጋዜጠኞች ኃላፊነት

ማንኛውም ጋዜጠኛ፡-

1. ትክክለኛና ከአድልዎ የፀዳ ዜናና ዘገባ ማቅረብ አለበት።
2. ምንጭ ያላቸው ስለመሆናቸው እርግጠኛ በሆነባቸው ፍሬ ነገሮች ላይ ብቻ የተመሰረቱ ዜናና ዘገባዎችን ማቅረብ አለበት።

3. ለዘገባው አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን ማስቀረት ወይም ማፈን የለበትም።

4. በእምነት የተሰጠ መረጃን ሚስጢራዊነት የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት።

5. የዘገባዎቹን ሚዛናዊነት መጠበቅ አለበት፡፡ በእጩ ተወዳዳሪዎች መሀከል መወቃቀስና መወነጃጀል ሲከሰት ጋዜጠኛው በተቻለው ሁሉ የሁለቱንም ወገኖች አስተያየት ያካተተ ዘገባ ማስተላለፍ አለበት።

6. ጎጂ ስህተት እንዳለበት የታወቀ ማንኛውንም የታተመ መረጃን በተቻለ ፍጥነት የማረም ወይም የማስተካከል ሀላፊነት አለበት፡፡

7. በሚቻለው ሁሉ የምርጫ ተወዳዳሪዎችንም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አስተያየት በሌሎች ወገኖች ብለዋል ተብሎ እንደተገለፀው ሳይሆን በቀጥታና ራሳቸው የተናገሩትን ቃል በቃል ማስተላለፍ አለበት።

8. ዘርን፣ ጾታን፣ የፍትወት ዝንባሌን፣ ሀይማኖትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት አመለካከት፣ ብሄራዊ ወይም ማህበራዊ አወጣጥን ጨምሮ በሌላ ማንኛውም አቋም ላይ የተመሰረተ አድልዎን ወይም አመፅን የሚያራግቡ ስሜታዊ አገላለፆችን መጠቀም የለበትም ፡፡

9. አድልዎን፣ ልዩነትን ወይም አመጽን የሚቀሰቅሱ ወገኖችን አመለካከት ሲዘግብ ይህን ምግባር ለማጋለጥ በሚያስችል አግባብ ማቅረብና የአስተያየቱ ወይም የቅስቀሳው ኢላማ የሆኑ ወገኖችን አስተያየትም ማካተት ይኖርበታል።

10. ከማንኛውም ፓርቲ፣ እጩ ተወዳዳሪም ሆነ ግለሰብ ማንኛውንም አይነት መደለያ ወይም ማግባቢያ መቀበል የለበትም፡፡

11. የዘገባውን ይዘት በሚመለከት ለማንኛውም ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ ቃል መግባት የለበትም፡፡

12. የህዝብ አስተያየት ዳሰሳ ወይም ጥናት ግኝቶችን በሚዘግብበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ የሚያስተላልፈው ዘገባም በተቻለ መጠን፦

ሀ/ ጥናቱን ማን እንዳስጠናውና በማን እንደተከናወነ

ለ/ ምን ያህል ሰዎች ቃለ መጠይቅ እንደተደረገላቸው፣ የት እና እንዴት ቃለ መጠይቁን እንደሰጡ፣ እንዲሁም በግኝቱ ላይ ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ስህተት መጠን፣

ሐ/ የቀረቡትን ጥያቄዎች ቃል በቃል የሚያሳዩ መረጃዎችን ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

13. የሚከተሉትን ድርጊቶች ግዙፍ የሙያ ጥፋቶች መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የሌላውን የስራ ውጤት እንደራስ አድርጎ ማቅረብ

ለ/ በተንኮል የሆነውን እንዳልሆነ አዛብቶ ማቅረብ

ሐ/ አሉባልታ፣ ዘለፋ፣ በሃሰት ስም ማጥፋት የሃሰት ውንጀላ

መ/ ማንኛውንም አይነት መደለያ ወይም ጉቦ መቀበል

## አንቀጽ 7. የመገናኛ ብዙኃን ኃላፊነት

1. ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን፡ የፍሬ ነገር ዘገባን እና አስተያየትን በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት:: የዜና ዘገባ ጋዜጠኛው እውነታውን በሃቅ የተገነዘበበትን ሁኔታ ማንፀባረቅ አለበት፡፡ አስተያየት ግን የህትመቱን ኤዲቶሪያል አቋም ሊያንፀባርቅ ይችላል ::

2. የህዝብ መገናኛ ብዙሃን በርእሰ አንቀፆቻቸው ላይ ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ሃሳብ ወይም አስተያየት ማቅረብ የለባቸውም ፡፡

3. መገናኛ ብዙሃን ሚዛናዊና ገለልተኛ የምርጫ ነክ ዘገባዎችን የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ለምርጫ ውድድር ነፃ የአየር ሰአት

አገልግሎት ወይም አምድ ሲያቀርቡም በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም በእጩ ተወዳዳሪዎች መሃል አድልዎ ወይም ልዩነት ማድረግ የለባቸውም ።

4. መገናኛ ብዙሃን ተቋማት የፖለቲካ ማስታወቂያዎችን በክፍያ ሊያስተናግዱ ከፈለጉ ሁሉንም ፓርቲዎች ያለአድልዎ ማገልገልና ለሁሉም እኩል በሆነ ክፍያ መሆን አለበት፡፡

5. የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የሚተላለፉ ዜናዎች፣ ቃለመጠይቆች እና ወቅታዊ ዘገባዎች አንድን ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ከመደገፍ ወይም ከመጥላት የሚነሱ መሆን አይኖርባቸውም::

6. የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣እጩ ተወዳዳሪዎች እና መድረኮቻቸው ፍትሃዊና ቋሚ የዘገባ ሽፋን መስጠት አለባቸው።

7. መገናኛ ብዙሃን ተቋማት መራጮች ሀሳባቸውንና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታትና እድሉንም መስጠት አለባቸው::

8. መገናኛ ብዙሃን ተቋማት ስለዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት ህብረተሰቡን ማስተማር ይኖርባቸዋል።

9. በታተመው ወይም በተሰራጨው ዘገባ ስሙ መጥፋቱን ወይም ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አስመልክቶ ምክንያታዊ ቅሬታ ካቀረበ በዚያው ሚዲያ መልስ የመስጠት ወይም ማስተካከያ የማውጣት መብቱ በብሮድካስተሩ ወይም በአሳታሚው መከበር ይኖርበታል። የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቱም በተቻለ ፍጥነት የቀረበለትን አስተያየት ብሮድካስት የማድረግም ሆነ የማተም ግዴታ አለበት::

10. መደበኛ የመንግስት ስራ ክንዋኔዎችን ሳይሆን ፖለቲካዊ ውዝግብ ያስነሱ ጉዳዮችን በሚመለከት በርዕሰ መንግስቱ፣ በሚኒስትሮች ወይም በፓርላማ አካላት የሚዘጋጁ የፕሬስ መግለጫዎች ወይም ለህዝብ የሚደረጉ ንግግሮች የዜና ሽፋን አሰጣጥ ምላሽ የመስጠት መብትን ወይም የእኩል ጊዜ አጠቃቀም ህግን መሰረት በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ይህ ግዴታ በተለይ መግለጫውን ወይም ማብራሪያውን የሚሰጠው ባለስልጣን የምርጫ ተወዳዳሪ

በሚሆንበት ጊዜ በጥብቅ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

11. የህዝብ ሚዲያ መራጩን ህብረተሰብ ለማስተማር የተዘጋጁ ማስተማሪያዎችን ብሮድካስት የማድረግ ወይም አትሞ የማሰራጨት ግዴታ አለባቸው::

12. መራጩን ለማስተማር የሚወጣ ማቴሪያል የተሟላና ትክክለኛ መሆን ይኖርበታል:: ለመራጩ ህዝብ ድምጽ የመስጠትን ጥቅም ጨምሮ የድምጽ አሰጣጡ ሁኔታ፣ መቸ እና የት የመራጮች ምዝገባ እንደሚደረግ ምዝገባውንም እንዴትና የት ማረጋገጥ እንደሚቻል፣ እንዲሁም ድምጽ መቸና እንዴት እንደሚሰጥ፣ የድምጽ አሰጣጡን ሚስጥራዊነትና ድምፅ የመስጠት ጠቀሜታን ውድድር የሚደረግባቸው የስልጣን አካላትና ተግባራቶቻቸውን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የተሟላ መረጃ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል::

13. የመራጮች ትምህርት አናሳና በታሪክ አጋጣሚ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋ በተዘጋጀ ፕሮግራሞችን ያካተተና እንዲሁም በባሕላዊ ተጽእኖ ምክንያት ከፖለቲካ ተሳትፎ የተገለሉ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል::

14. የሚዲያ ተቋማት የሚያስተላልፏቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች የስነምግባር መመሪያ ደንቡን መስፈርቶች የጠበቁ መሆናቸውን ዘወትር መከታተል ይኖርባቸዋል::

**አንቀፅ 8.** የፖለቲካ ፓርቲዎች

1. የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎች የሚዲያ ተቋማትን ነፃነት ማክበር ይኖርባቸዋል::

2. የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎች የጋዜጠኞችን ስራ የሚያውክ ወይም የሚያሰናክል ተግባር መፈፀም የለባቸውም::

3. በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲም ሆነ እጩ ተወዳዳሪዎች ስልጣናቸውን ተጠቅመው የተለየ የሚዲያ የአየር ሰዓት ለማግኘት ሙከራ ማድረግ የለባቸውም:: ይህ አንቀፅ በሁሉም መገናኛ ብዙሃን ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን በተለይም ደግሞ የህዝብ መገናኛ ብዙሃኑ በስልጣን ላይ ባለው የህግ አስፈፃሚ አካል ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር የሚገኙ ከሆነ በነዚህ ተቋማት ላይ የበለጠ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. ፓርቲዎችም ሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎች ለጋዜጠኞች ወይም ለሚዲያ ተቋማት ጉቦ ወይም መደለያ በመስጠት የተለየ ተጽእኖ በማድረግ በምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ዝግጅቶች ወይም ሁነቶች ላይ እንዲገኙ ወይም ስለነሱ አዎንታዊ ዘገባ እንዲያቀርቡላቸው ወይም በሌላ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ ላይ አሉታዊ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማበረታታት ወይም ማግባባት የለባቸውም ፡፡

5. የፖለቲካ ፓርታዎችና እጩዎች ያለአግባብ የሌሎች ፓርቲዎችን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎችን አቋም ያለ አግባብ አዛብተው ማቅረብ ወይም ሌሎች ፓርቲዎችን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎችን የሚመለከቱ ማንኛቸውም አይነት የተሳሳቱ የፍሬ ነገር መረጃዎችን መረጃ ማቅረብ የለባቸውም፡፡

6. ፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎች ግጭትን የሚቀሰቅሱና የሌላውን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፉ ወይም የሚያዋርዱ ቃላቶችና አነጋገሮችን ከመጠቀም መቆጠብ ይኖርባቸዋል።

7. የፓርቲ አመራሮች በዚህ የስነ ምግባር ደንብ ውስጥ የሰፈሩት የነፃ ክርክርና የመቻቻል እሴቶች ለምርጫ ዘመቻ ሠራተኞቻቸው እንዲያውቋቸው መደረጉንና ማብራሪያም ያገኙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡ ፓርቲዎች በነሱ ስም የቅስቀሳ ስራ ለሚያከናውኑ ወገኖች ንግግርና ድርጊት ሙሉ ሃላፊነት መውሰድ ይኖርባቸዋል።

## አንቀፅ 9. የምርጫ አስፈፃሚ አካላት

1. የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የኤዲቶርያል ነፃነትን ጨምሮ የሚዲያ ተቋማትን ነፃነትና የፖለቲካዊ ወገንተኛነትን የመግለፅ መብት ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

2. የምርጫ አስፈፃሚዎች የፓርቲዎችንና የእጩ ተወዳዳሪዎችን ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

3. የምርጫ አስፈፃሚዎች ምርጫውን በግልጽና በታማኝነት ማከናወን አለባቸው፡፡

4. የምርጫ አስፈፃሚዎች የስራ ክንዋኔያቸው ሙሉ ለሙሉ ለሚዲያ ምርመራ ግልፅ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው::

5. የምርጫ አስፈፃሚዎች በክፍያ የሚደረግ ማስታወቂያም ሆነ በነፃ የሚሰጥ መረጃን በተመለከተ በመገናኛ ብዙሃን መሀከል አድልዎ መፈፀም የለባቸውም::

6. የምርጫ አስፈፃሚዎች ህብረተሰቡ በእውቀት ላይ ተመስርቶ የመምረጥ መብቱን ተግባራዊ እንዲያደርግ ለማስቻል ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ማስተላለፍ አለባቸው::

7. የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የምርጫ ሂደቱን ቀናነት ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለምሳሌ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችንና የድምጽ ቆጠራውን ሂደት በሚመለከቱ የመገናኛ ብዙሃን የዜና ዘገባዎች ላይ ገደቦችን ሊያበጁ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 10. የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ 11. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በቦርዱ ከጸደቀበት ከሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መርጋ በቃና (ፕሮፌሰር)
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
ሰብሳቢ